# ህወሀትን በተመለከት  ምን ይደረግ፣ ሕዝቡ ምን ይላል?

**ከጁላይ 10፣ 2020 እስከ  ረብኡ ጁላይ 15፣ 2020የተካሄደ የዳሰሣ ጥናት ግኝትች**

**ጁን 19፣2020**

በሀገራችን በኢትዮጲያ ውስጥ ህወሀት መራሽ መንግስት ለ27 ተከታታይ አመታት በስልጣን ላይ ቆይቷል። ህወሀት በህዝብ ትግል ከአዲስ አብባው ስልጣኑ ተባሮ  መቀሌ ከመሸገ ወዲህ እየቆየና እያደር አብሮት ከነበሩት ሌሎች የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች ጋር ሳይቀር አየተቀራረበና ልዩነቱንም እያጠበበ ከመሄድ ይልቅ በየጊዜው የተካረረ ቀራኔ ወስጥ እየገባ ይገኛል።

እንዳለፉት 28 እመታት ሁሉ አሁንም ትግራይን ለብቻው በማስተዳደር ላይ የሚገኘው ህወሀት ባላፉት ጥቂት ወራት የመአከላዊ መንግስቱን (የፌደራል መንግስቱን)ወሳኔዎች ከመቃወም አልፎ የፊደራል መንግስቱን ሙሉ በሙሉ  " በአምባገነንነት ፈርጆ" እርሱንም ለማስወገድ ሰፊ የቅስቀሳ ሰራ እየሰራ ይገኛል።

በቅርቡ የሀገር አቀፉ የፓርላማ ምርጫ መራዘምና የአርቲስት ሀጫሉ ሁንዴሳን ግድያ ተከትሎ ህወሀት   ከፊደራል መንግስቱና ከገዥው የብልጽግና ፓርቲ ጋር  ይበልጥ ወደ ተካረረ ቅራኔ ገብቷል።

ህወሀት የህዝብ ድጋፍ አለኝ አሁንም የኔን ራአይ ህዝብ ይደግፋል ይላል። ትላንትም ዛሬም ተወዳጅ ነኝ ይላል። በሌላ በኩል ሌሎች ይህ ሀስት ነው ህውሀት እጅግ የተጠላ ድርጅት ነው ያላሉ፡ ህወሀት ከፋፋይና አጥፊ ድርጅት ነው ይላሉ። በአሁኑ ሰአት በሀገሪቱ የተላያዩ ቦታዎች የሚታዩት ግጭቶችና አለመረጋጋቶች   በቀጥታም ይሁን በተዛዋሪ የህወሀት  እጅ አለበት  የሚለው አመለካከት በስፊው ይደመጣል።

እነዚህንና  ሌሎችንም ሁኔታዎች በሚታዩበት በአሁኑ ሰአት  የህዝቡ አመለካከት ምንድን ነው ፣ የሚለውን  በአራት ቁልፍ ጥያቄዎች ዙሪያ በዚች አጭር የዳሰሣ ጥናት ለማየት ሞክሬአለሁ።

## ጥናቱ እንዴትና መቼ ተካሄደ

ጥናቱ የተካሂደው ከቅዳሜ ጁላይ 10፣ 2020 ሌሊት ጀምሮ እስከ  ረብኡ ጁላይ 5፣ 2020 ድርስ ለአራት ቀናት ነው። የተሳታፊዎችን አመለካከት ለመስብስብ የተጠቀምኩበት  መደበኛ የፌስ ቡክ ን ነው። መጠይቁ ከተዘጋጀ በኹላ በፌስቡክ እንዲሰራጭና ታዳሚወችም አስተያየታቸውን መጠይቁን በመሙላት  እንዲያካፍሉ ተጠይቀዋል።

ይህ መጠይቅ በፌስ ቡክ ለሁሉም በይፋ (public) የተለቀቀ በመሆነ የተለያየ ፖለቲካ እመለካከት ያላቸው ሁሉ የመሳተፍ አድል አግኘተዋል ብየ አስባለሁ።

የተጠቀምኩበት የስርቬይ ፐሮግራም  በአንድ ኮምፒዩተር ከአንድ ጊዜ በላይ መጠይቁን መሙላት ሰለማይፈቅድ አንድ ስው በዛ ያለ ጊዜ መጠይቁን በመሙላት የድምጹን ውጤት ወደአንድ አቅጣጫ እንዲያዘነብል የማድረጉ እድሉ እጅግ ዝቅተኛ ነበር፡

የዳሰሳው ትኩረት በህወሀት ላይ ያለውን አስተያየት መቃኘት በመሆኑ  የትግርኛ ተናጋሪ ወገኖቻችን የሚታደሙባቸው መድረኮች ላይ (ለምሳሌ፣ በትግራይ ሚዲያ ኔትወርክ፣ ) ይህ መጠይቅ ተሰራጭቷል፡

## የጥናቱ ተግዳሮቶች

የጥናቱ ድክመቶች ሁለት ነጥቦች ላይ ያተኮረ ነው አንደኛው በትክክልም የ random sampling ቴክኔክ አልተከተለም እና  ሙሉ ለሙሉ የህዝቡን ስሜት የማንጽባረቅ ችሎታው በተወስነ ደረጃም ቢሆን ዝቅ ብሏል። ሆኖም ወጤቱ ከተመዘገበው  ከፍተኛ ወጤት ጋር ሲታይ ስህተቱ ጎላ ያለ ቢሆንም እንኳ የውጤቱ አስተማማኘነት እጅግ ሰፊ ነው ማለት ይቻላል። ይህም በመሆኑ በዚህ ጥናት የተመለከትው ግኝት መሉ በሙሉ የኢተዮጲያ ህዝበ እይታን ያሳያል ማለት አይቻልም ። የሚቻለው ጥናቱ የሚያሳየው የህዘቡ አመለካከት ወደየት ያዘነበለ እንደሆን አመላክች ነው ማለት ይቻላል።

ተመራማሪዎች ይህን ወደፊት በሚያካሂዱት ጥናት የዚህን ጥናት ደከመቶች አርመው  ተጭማሪ እየታን አዳባሪ ሰራ እንደሚያሳዩን ተስፋ አደርጋለሁ።

## የቀረቡ ጥያቄዎች

በጥናቱ ውስጥ ለማየት የፈለግነው  የሚከተሉትን አራት ነጥቦች በተመለከት ያለውን አመለካከት ነው

1. ሕወሀት ከሀጋዊ ፖለቲካ መድርክ መታገድ ስርትፊኬቱንም መቀማት አለበት
2. የህወሀት መሪዎች ንብረት እንዳይንቀሳቀስ መታገድ አለበት
3. የህወህት አካል የሆነው ኤፈርት ንብረት መታገድ አለበት
4. ክላይ የተጠቀሱት እርምጃውች ክመውሰዳቸው በፊት ይፋና የመጨረሻ ማስጠነቀቂያ ይሰጣቸው

ለእያንዳንዱ ጥያቄ በመልስነት የተስጡት  አማራጮች

- Yes አዎ እስማማለሁ
- No መሆን የለበትም   እና
- Undecided እርግጠኛ አይደለሁም/አልወስንኩም የሚሉ ናቸው።

## የጥናቱ ግኝቶች

የእያንዳንዱ ጥያቄ ግኝቶች የሚከተሉት ናቸው

### ጥያቄ አንድ ፡ሕወሀት ከሀጋዊ ፖለቲካ መድርክ መታገድ ስርትፊኬቱንም መቀማት አለበት

ለዚህ ጥያቄ መልስ ከስጡት 53 ተሰታፊውች ውስጥ

- Yes አዎ እስማማለሁ  94.34%
- No መሆን የለበትም   1.89 %
- Undecided እርግጠኛ አይደለሁም/አልወስንኩም የሚሉ ደግሞ 3.77% ናቸው

**1.** ሕወሀት ከሀጋዊ ፖለቲካ መድርክ መታገድ ስርትፊኬቱንም መቀማት አለበት

| | | | Response Percent | Response Total |
|---|---|---|---|---|
| 1 | Yes አዎ እስማማለሁ | | 94.34% | 50 |
| 2 | No  አልስማማም | | 1.89% | 1 |
| 3 | Undecided  እርግጠኛ አይደለሁም/አልወስንኩም | | 3.77% | 2 |

ይህ ግኝት ህዝብ በህወሀት ላይ ቅሬታው እጅግ ከፍተኛ መሆኑንና ከሀጋዊ የፖለቲካ መድረኩም ሙሉ በሙሉ ህገወጥ ተብሎ ቢገለል የጥናቱ ትሳታፊዎች ውስጥ ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ የሚደግፉ መሆኑንና ሊነሳ የሚችለው ተቃውሞም እጅግ ዝቀተኛ እንደሚሆን ያሳያል።

የኢትዮጳያ ህዝብ መድብለ ፓርቲ ተግባራዊ እንዲሆን ፣ የተለያዩ አመለካከቶች በፖለቲካው መድረክ እንዲንጸባረቁ ለረዥም ጊዜ ያደረገውን ተጋድሎ በግምት አስገብተን ስንመለከት፣ ይህ ሁኔታ ህወሀት በረዥም የገዥነት ታሪኩ ህዝብን በሰፈው ያማረረ ነበርና የዚህ ነጸብራቅ ሊሆን ይችላል። ሌሎች ከህውሀት ጋር አብረው ለ27 አመታት ሀገሪቱን የገዙ ክፍሎች በአንጻሩ የዚህ አይነት ቅቡልነት ማጣት እንደሌለባቸው ስንመለከት ደግሞ የዚህ እገዳ ድጋፍ ስፊ መሆን  ህወሀት በአሁኑ ሰአት እየወሰደ ያለው አቋም ሊሆን እንደሚችል ያመላክታል።

### ጥያቄ ሁለት ፡. የህወሀት መሪዎች ንብረት እንዳይንቀሳቀስ መታገድ አለበት

ለዚህ ጥያቄ መልስ ከስጡት 53 ተሰታፊዎች ውስጥ

- Yes አዎ እስማማለሁ 98.11%
- No መሆን የለበትም 1.89 %
- Undecided እርግጠኛ አይደለሁም/አልወስንኩም የሚሉ የሉም

| **2.** የህወሀት መሪዎች ንብረት እንዳይንቀሳቀስ መታገድ አለበት | | | Response Percent | Response Total |
|---|---|---|---|---|
| 1 | Yes አዎ | | 98.11% | 52 |
| 2 | No አልስማማም | | 1.89% | 1 |
| 3 | Undecided እርግጠኛ አይደለሁም/አልወስንኩም | | 0.00% | 0 |

ይህ ግኝት ሃሳባቸውን ካካፈሉት ውስጥ ከ2% በታች ከሚሆኑት ውጪ ሌሎች የህወሀት መሪዎን ንብረት እንዳይንቀሳቀስ ቢደርግ እንደሚደግፉ ያሳያል። ከላይ በቁጥር አንድ ላይ ከተነሳው ጥያቄ ጋር ተያይዞ ሲታይም፣ ከህውሀት በላይ በድርጅቱ መሪዎች ላይ ያለው ቅሬታ ይበልጥ ከፍ ያለ ( በ3.77%) እንደሆነ ያመላክታል።

**ጥያቄ ሶስት፡ የህወሀት አካል የሆነው ኤፈርት ንብረት መታገድ አለበት**

ለዚህ ጥያቄ መልስ ከስጡት 53 ተሰታፊዎች ውስጥ

- Yes አዎ እስማማለሁ 98.11% (13 ሰዎች)
- No መሆን የለበትም 1.89 %
- Undecided እርግጠኛ አይደለሁም/አልወስንኩም የሚሉ እልነበሩም

| **3.** የህወሀት አካል የሆነው ኤፈርት ንብረት መታገድ አለበት | | | Response Percent | Response Total |
|---|---|---|---|---|
| 1 | Yes አዎ | | 98.11% | 52 |
| 2 | No አልስማማም | | 1.89% | 1 |
| 3 | Undecided እርግጠኛ አይደለሁም/አልወስንኩም | | 0.00% | 0 |

ይህ ግኝት የጥናቱ ተሳታፊውች በህወሀት ስር የሚተዳደሩት ንብረቶች የህወሀት መጠቀሚያ ሆነው እንዳይቀጥሉ ቢደረግ እጅግ ሰፊ ደጋፍ እንዳለው ያሳያል።ጥያቄው ሰለመታገድ አንጂ ሰለመውረስ ሰላልሆን  በዚህ አኳያ የአተረጓጓም ጥንቃቄ ያስፍልጋል፡ በተጨማሪም ደርጅቶቹ ከታገዱ በኹላስ በማን ይተዳደሩ የሚለውን ሰላልዳሥኩ ከዚህ ጥናት ተነስቶ ማጠቃለያ ላይ መድረስ አይቻልም።

## ጥያቄ አራት፡ክላይ የተጠቀሱት እርምጃውች ክመውስዳቸው በፊት ይፋና የመጨረሻ ማስጠነቀቂያ ይሰጣቸው

ለዚህ ጥያቄ  መልስ ከስጡት 53 ተሰታፌውች ውስጥ

- Yes አዎ እስማማለሁ  28.85% (15 ስዎች)
- No መሆን የለበትም   67.31%  (35)
- Undecided እርግጠኛ አይደለሁም/አልወስንኩም የሚሉ ደግሞ 3.85% ( 2 ስዎች) ናቸው

**4.** ክላይ የተጠቀሱት እርምጃውች ክመውስዳቸው በፊት ይፋና የመጨረሻ ማስጠነቀቂያ ይሰጣቸው

| | | | Response Percent | Response Total |
|---|---|---|---|---|
| 1 | Yes አዎ | | 28.85% | 15 |
| 2 | No  አልስማማም | | 67.31% | 35 |
| 3 | Undecided እርግጠኛ አይደለሁም/አልወስንኩም | | 3.85% | 2 |

የተሳታፊዎች አመለካከት የህወሀትን መታገድ፣ የመሪዎቹንም ንብረት ማገድና ድርጅቱ በስሩ የሚያንቀሳቀስውን ኤፈርትን ማገድ እጅግ ከፈተኛ የሆን ድጋፍ ሲኖረው  ቀጥተኛ እርምጃ ለመውስድ ግን ከተሳታፊዎች ውስጥ 28.85% ወደ አንድ ሶስትኛ የሚጠጉት ህወሀቶች የመጨርሻ ማስጥንቀቂያ ይስጣቸው የሚሉ ሲሆኑ 67.31% ማለትም ክሶስት ስው ሁለቱ ግን ካሁን በኋላ ማስጠንቀቂያ መስጠት አያስፈልግም ይላሉ።

ማስጠንቀቂያ ይሰጣቸው የሚሉት ክፍሎች ምናልባትም  ይህ ማስጠንቀቂያ ቢሰጣቸው የህወሀት መሪዎቹ ከአፍራሽ ስራቸው ይቆጠቡ ይሆናል ከሚል ግምት በመነሳት ሊሆን ይችላል።

ሌሎቹ ደግሞ ህወሀት አቋሙን እንዲያሰትካክል እስካሁን በቂ እድል ተስጥቶታልና ካሁን በኋላ ጊዜ ማባከን  አይገባም ከሚል እሳቤ ተነስትወ ሊሆን ይችላል።

ያም ሆነ ይህ ሁለቱ መልሱች የሚቃረኑ ሳይሆኑ የሚጣጣሙ ናቸው። ልዩነት ያለ የሚመስለው የመጨርሻውን እርምጃ ከመውሰድ በፊት የመጨረሻ ማስጥንቀቂያ በማስጠትና ባለምስጠት ላይ ብቻ ነው።

**ማጠቃለያና ቀጣዩ ተግባር**

ይህ ጥናት ህዝብ በህወሀት ላይ ያለው ቅሬታ እጅግ ስፊ መሆኑን ያሳያል። የዚህ አይነት ሰፊ የህዝብ ቅሬታ ያለበት የፖለቲካ ድርጅት ራሱን ተቀባይ ለማድረግ የሚኖርበትን ከፍትኛ የአቀበት ጉዞም ያመለክታል።

ህወሀት በአሁኑ ሰአት በሀገራችን ፖለቲካ ውስጥ የሚወስዳቸው የፖለቲካ አቋሞች ምንም የህዝብ ድጋፍ እንደሌላችወም ያመላክታል። የፖለቲካ አቋሙ ቢያንስ የተወሰነ  ድጋፍ ቢኖረው ይህ ድርጅት ከህጋዊ ፖለቲካ መድረኩ ይታገድ ህጋዊ ስርቲፊኬቱንም ይነጠቅ የሚለው ዝቅ ብሎ ይታይ ነበር።

ይህን ጥናት እንደአምላካች ስንወስድ በነጻነት ሀሳቡን መገለጽ ቢችል የህወሀት ቦታ በትግራይ ውስጥ ምን ሊሆን ይችላል? የሚለውን ጥያቄ ደግሞ ደጋግሞ ለመጥየቅ ያስገድዳል።

በመጨረሻም ህሕውሀት ላይ ያለውን ስፌ እወንታዊ አመለካከት ሰናጤን  በተዛዋሪም ከህወሀት ጋር የወዳጅነት ቅርርብን የሚያሳዩ ድርጅቶችም ሊደርስባቸው የሚችለው ተቃውሞ ቀላል ሊሆን እንደማይችል መገመት ይቻላል።

በአጠቃላይ በሀገራችን ፖለቲካ የህዝብ አመለካከት ጥናት ማካሄድና ይህንንም ለተግባራዊ እንቀስቃሴ ግብእትነት መውሰድ ያልተለመደ ነው። ይህ ደግሞ በከፊል ለረጅም አመታት ህዝባችን ካሳለፋቸው እሳዛኝ የፖለቲካ ተጸእኖወችና ስሜቱን በትክክል መግለጽ ያስከትል ከነበርው ክፍተኛ ዋጋ ጋር የተዛመደ ሊሆን ይችላል፡ይህ ሰነ ልቦና ለብዙ ነገር እንቀፋት ነውና ሊሰበር ፣ ሊቀየር ይገባል።

ይህ ጥናት እጅግ የተሟላ ነው ባልልም የሀገራችንን ፖለቲካና የህዝብ አስተሳሰብን በመገንዘብ በኩል የተወስነ አስተዋጻኦ ያበረክታል ብየ አስባለሁ። ሌሎች ባለመያዎች ሰፌና ጠለቅ ያለ ጥናት በማካሄድና ወጤቱንም ይፋ በማድረግ የሀገራችን ፖለቲካ በመረጃ ላይ የተመረኮዝ እንዲሆን የበኩላቸውን አሰተዋጻኦ እንደሚያደርጉ ተስፋ አደርጋለሁ።